የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

አስራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፸፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 74
ADDIS ABABA 7[th] June 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፯/፳፻፫ ዓ.ም.
የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ስርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ …………ገጽ ፭ሺ፱፻፳፬

## CONTENTS

Regulation No. 207/2011
Code of Practice of the Floriculture Sector Council of Ministers Regulation ........Page 5924

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፯/፳፻፫**

**የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የማይፈለጉ አካባቢያዊና ማሕበራዊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት የሚያስችሉ የግብርና አሠራሮችን በአበባ ልማት ዘርፍ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ፤

አካባቢያዊ አዛላቂነት እና ማሕበራዊ ተቀባይነት ያለው የግብርና አሠራርን ምንነት መግለፅ እና መደንገግ የአበባ ኢንዱስትሪን አዛላቂነት ስለሚያጎለብት፤

የኢትዮጵያ የአበባ ኢንዱስትሪን መልካም ዝና ከፍ ለማድረግ እንዲቻል የማሕበራዊ እና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃዎችን የሚወስን የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፪ አንቀፅ ፭ እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/ ፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአበባ ልማት ዘርፍ የአሠራር ሥነ ምግባር ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፯/፳፻፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/ ፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፫ መሰረት የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 207/2011**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE THE CODE OF PRACTICE OF THE FLORICULTURE SECTOR**

**WHEREAS** the implementation of good agricultural practices in the floriculture sector is necessary to avoid undesirable environmental and social impacts;

**WHEREAS** it is necessary to define and regulate the essential elements of environmentally sustainable and socially acceptable agricultural practices to enhance the sustainability of the floriculture industry;

**WHEREAS** the need to enhance the reputation of the Ethiopian floriculture industry calls for the issuance of a certification system that determines the level of compliance with the requirements of environmental and social responsibility;

**NOW, THEREFORE,** this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 20 of the Environmental Pollution Control Proclamation No.300/ 2002.

## PART ONE

## GENERAL

**1.. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Code of Practice of the Floriculture Sector Council of Ministers Regulation No. 207/2011".

**2. Definition**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Authority" means the Environmental Protection Authority established pursuant to Proclamation No.295/2002;

የአንዱ ዋጋ Unit Price 5.80

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Federal Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፪/ "የምስክር ወረቀት" ማለት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለሚያሟላ እርሻ ባለሥልጣኑ የሚሰጠው በነሐስ፣ በብር ወይም በወርቅ ደረጃ የተመደበ የማሕበራዊና አካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃ ማረጋገጫ ሠነድ ነው፤

፫/ "እርሻ" ማለት ተቆርጦ ለገበያ የሚውል አበባን፣ ለማስዋብ የሚውል ተክልን ወይም የአበባ ዘርን በማምረት ላይ የተሰማራ ኩባንያ ነው፤

፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. ዓላማ

የዚህ ደንብ ዓላማ የማሕበራዊና አካባቢያዊ አዛላቂነት ግጴታዎችን የማስተግበር እና የእርሻዎችን አመራረት፣ የምርት ጥራትና የገበያ ተወዳዳሪነት ማሻሻል ነው፡፡

## ፬. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የማሕበራዊና አካባቢያዊ ኃላፊነቱን ስለመወጣቱ የምሥክር ወረቀት ያልተሰጠው እርሻ በአበባ ልማት ዘርፍ መሰማራት አይችልም፡፡

፪/ ይህ ደንብ ተቆርጦ ለገበያ የሚውል አበባን፣ እንዲሁም የአበባ ዘር ማባዛትን ጨምሮ ለማስዋብ የሚውል ተክልን በሚያመርት እርሻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎች

## ፭. የነሐስ ደረጃ

በዚህ ደንብ መሠረት በምርት ሂደት ለመቀጠል የሚፈለገውን የነሐስ የማሕበራዊና የአካባቢያዊ የኃላፊነት ደረጃ ስለማክበሩ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚፈልግ እርሻ ፡-

፩/ በጥቅም ላይ እንዳይውሉ በተከለከሉም ሆነ ባልተመዘገቡ የግብርና ኀጥረ ነገሮች አለመጠቀም፤

፪/ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የቆሻሻ አያያዝ ሥርዓትን መከተል፤

፫/ የአካባቢና የሥራ ቦታ ደህንነት ጠንቆችን መገምገም፤

፬/ ደህንነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ኀጥረ ነገሮችን ማከማቸትና መጠቀም፤

2/. "certificate" means a document granted by the Authority attesting the level of social and environmental compliance of a farm with the provisions of this Regulation and consists of a Bronze, a Silver or a Gold level of excellence;

3/ "farm" means a company engaged in the prod -uction of cut flowers, ornamental plants or flower seedling;

4/ "person" means any natural or juridical person;

5/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Objective

The objective of this Regulation is to realize environmental and social sustainability and to improve the performance and market competitiveness of farms.

## 4. Scope of Application

1/ Any farm that has not obtained a certificate regarding its compliance with environmental and social responsibilities under this Regulation shall not engage in farming.

2/ This Regulation shall apply on a farm engaged in the production of cut flowers, including other ornamental plants or flower seedlings.

## PART TWO
## COMPLIANCE LEVELS OF SOCIAL AND ENVIRONMENTAL RESPONSIBILITIES

## 5 Bronze Level

Farms intending to obtain a certification of social and environmental compliance at a Bronze Level, which is the minimum standard for allowing production to continue under this Regulation, shall:

1/ use neither banned nor un-registered agro-chemicals;

2/ put in place environmentally sound waste management practices;

3/ assess risks related to environment and occupational safety;

4/ ensure safe agrochemical storage and use;

፭/ በእርሻ ቦታው ወይም ከአካባቢው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመተባበር የሕክምና ግልጋሎት ለሠራተኞች ማቅረብ፤ የስራ አካባቢ ጤናማነትን ማረጋገጥ፤

፮/ የሠራተኞች የመደራጀት መብትን፣ በሕብረት የመደራደርን እና ከሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች መብቶችን የሚያራምድ ተገቢ የሥራ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ፤

፯/ ተባይ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች በግብርና ንጥረ ነገሮች አያያዝ እንዲሁም በመከላከያና በእጥበት መሣሪያዎች አጠቃቀም የሰለጠኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

፰/ አካባቢያዊ፣ ማሕበራዊና የጤና ግዴታ ማሟላቱን ለመገምገም የሚያስችለውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፤

፱/ የውሃ ፍጆታውን፣ በግብርና ንጥረ ነገሮች አጠቃቀሙን፣ የቆሻሻ አያያዙንና የሃይል ፍጆታውን መለካት፣ መገምገምና ዘገባ ማቅረብ፤

፲/ የአደጋና የአስቸኳይ ጊዜ ስርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ማረጋገጥ፤

፲፩/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፰)፣ (፱)፣እና (፲) መሠረት በተካሔደው ቁጥጥር መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ፤

፲፪/ ሠራተኞቹን በአዛላቂ አካባቢያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ ማሰልጠን፤

፲፫/ አግባብነት ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚወሰኑ ማናቸውም ተጨማሪ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና የጤና መስፈርቶችን ማሟላት፤

አለበት፡፡

## ፮. የብር ደረጃ

፩/ የብር ደረጃን ለማግኘት የሚፈልጉ እርሻዎች ለዚህ ደረጃ ኦዲት በሚደረጉበት ጊዜ የነሐስ ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪/ የብር ደረጃ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ከነሐስ ደረጃ መስፈርቶች በተጨማሪ በእርሻው የማሕበራዊ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ፡-

ሀ) በዓለም አቀፍ ገበያ በወቅቱ የሚፈለጉ ተገቢ የግብርና አሰራር ግዴታዎችን የማክበር፤

ለ) የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ አያያዝ የአሰራር ብቃቱን በየጊዜው ለመገምገም የሚያስችል ተቀባይነት ያለው የኦዲት ሥርዓትን የመዘርጋት፤

ሐ) አዋጪ የውኃ አጠቃቀም በጎ ተሞክሮዎችን ተፈፃሚ የማድረግ፤

መ) የድህረ ምርት አያያዝ በጎ ተሞክሮዎችን እና ተቀባይነት ያለው የፀረ ተባይ የመጠን ደረጃዎችን የማክበር፤



5/ ensure the provision of medical services at the farm or in cooperation with local service providers as well as maintain good occupational health;

6/ ensure good labour conditions, including the right of workers to organize, engage in collective bargaining and other work-related rights;

7/ ensure that personnel working on pest control activities are trained on the safe handling of agrochemicals and the use of appropriate protective devices and washing facilities;

8/ put in place its own system of monitoring in order to ensure its compliance with environmental, social and health requirements;

9/ measure, evaluate and report on its performance relating to its consumption of water, use of agrochemicals, management of waste and consumption of energy;

10/ put in place and ensure the implementation of accident and emergency procedures;

11/ undertake the required remedial action indicated by the monitoring and evaluation report provided for under sub-Articles 3, 8, 9 and 10 of this Article;

12/ provide training to its employees on environmental and social sustainability issues;

13/ fulfill any additional environmental, social and health requirements issued by the appropriate government agencies.

## 6. Silver Level

1/ Farms wishing to achieve compliance at the Silver Level are required to demonstrate compliance with all the requirements at the Bronze Level at the time of auditing for the Silver Level.

2/ Compliance with the Silver Level ensure that the social and environmental management plan of the farm complies with the following requirements in addition to those specified for the Bronze Level:

a) meet good agricultural practices required by the prevailing international market;

b) put in place an acceptable auditing system that allows periodic evaluation of its social and environmental management practices;

c) comply with good practices that ensure efficiency of water use;

d) comply with good practices on post harvest practices and accepted pesticide residue levels;

ሠ) ለጎብኚዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ ዎች የቅሬታ ማቅረቢያ እና ምላሽ መስጫ ሥርዓት የመዘርጋት፣

ተጨማሪ ግዴታዎችን ማሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

፯. **የወርቅ ደረጃ**

፩/ የወርቅ ደረጃን ለማግኘት የሚፈልጉ እርሻዎች ለዚህ ደረጃ ኦዲት በሚደረጉበት ጊዜ የብር ደረጃ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪/ የወርቅ ደረጃ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ለማሟላት ከብር ደረጃ መሥፈርቶች በተጨማሪ በእርሻው የማሕበራዊና አካባቢያዊ አያያዝ ዕቅድ፡-

ሀ) በገጠር ወይም በከተማ ማህበረሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የክህሎት ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን፣

ለ) የማህበረሰቦችን፣ የትምህርት ቤት የአካባቢ ክበቦችን እና ሌሎች የአፈር መከላትን ለመከላከል፣ የእጽዋት ሽፋን እንዲጨምር ለማድረግ፣ የውሃ አዘል መሬቶችን እና ሃይቆችን አቅም ለማጎልበት፣ ብዝሃ ሕይወትን ለመንከባከብ እንዲሁም የወንዞችን፣ የከርሰ ምድር ውሃንና የአየርን ጥራት ለማሻሻል የታለሙ ተግባራትን፣

በገንዘብ የማገዝ ተጨማሪ ግዴታዎችን ማሟላት አለባቸዉ፡፡

**ክፍል ሦስት**

**አረጋጋጮችን ስለመሰየም**

፰. **በአረጋጋጭነት ለመሰየም ማመልከቻ ስለማቅረብ**

አረጋጋጭ ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ድርጅት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም ብቃቱ ተገምግሞ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው፡-

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች ያሉት መሆኑን፣

፪/ የሥራ ማከናወኛ የውስጥ የአሰራር ስርዓትን መዘጋጀቱን፣

፫/ እንዲያከናውነው ከተሰጠው ተግባር ጋር የጥቅም ግጭት የሌለው መሆኑን፣

፬/ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመማከር ከሚወስነው የአገልግሎት ክፍያ ጣሪያ ሳያልፍ አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኑን፣

የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

e) put in place a complaint and response procedure including for visitors and other stakeholders.

7. **Gold Level**

1/ Farms wishing to achieve compliance at the Gold Level are required to demonstrate compliance with all the requirements of the Silver Level at the time of auditing for the Gold Level.

2/ Compliance with the Gold Level ensures that the social and environmental management plan of the farm complies with the following requirements in addition to those specified for the Silver Level:

a) support urban or rural local communities through financing demand driven skill enhancement programmes ;

b) finance community, school environment clubs and other initiatives that are designed to prevent soil erosion, to enhance vegetation cover and carrying capacity of lakes and wetlands, to conserve biodiversity and to improve the quality of rivers, groundwater and air.

**PART THREE**

**DESIGNATION OF VALIDATORS**

8. **Application to Obtain the Status of a Validator**

Any firm that intends to be a validator shall provide documents substantiating the following to enable the Authority to issue it with a certificate upon assessing its competence:

1/ have the required employees that have the necessary competence to perform the tasks required under this Regulation;

2/ prepare internal procedures for carrying out its functions;

3/ demonstrate that it has no conflict of interest with the activities for which it has been selected to carry out;

4/ express its consent to provide any service without exceeding the cap on the service fee that shall be determined by the Authority in consultation with the concerned entities.

፱. <u>የአረጋጋጭ ተግባራት</u>

፩/ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በባለሥልጣኑ የተመዘገበ አረጋጋጭ:-

ሀ) የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለባለሥ ልጣኑ በሚቀርቡ ሠነዶች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን በመመርመር አካባቢያዊ አዛላቂነታቸውንና ማሕበራዊ ተቀባይ ነታቸውን የማረጋገጥ፤

ለ) የምስክር ወረቀት ለማግኘት አመልካቹ ያቀረበውን የማሕበራዊና የአካባቢያዊ አያያዝ ዕቅድን መርምሮ የማሕበራዊና የአካባቢ የሃላፊነት ደረጃውን የማረጋገጥ፤

ሐ) አመልካቹ በማሕበራዊ እና በአካባቢያዊ አያያዝ ዕቅዱ ላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን ለመፈፀም ያለውን አቅም የማረጋገጥ፤

መ) የአመልካቹን የማሕበራዊ እና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃ የሚመለከት የውሳኔ ሃሳብ ለባለስልጣኑ የማቅረብ፤

ሠ) ለባለሥልጣኑ ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ዘገባ የማቅረብ፤

ተግባራት ለማከናወን ይችላል፡፡

፪/ አረጋጋጩ የዚህን ደንብ አፈፃፀም የሚመለ ከቱትን መዛግብትንና ሌሎች ሠነዶቹን ቢያንስ ለሁለት ዓመት ማስቀመጥ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

፲. <u>የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩/ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚያሟላ ማንኛውም እርሻ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም እርሻ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶና ከቅፁ ጋር ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ያዘጋጀውን የማሕበራዊ እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲሁም በታወቀ ገለልተኛ ኦዲተር የተመሰከረለት የፋይናንስ ኦዲት ዘገባውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም እርሻ የሥራ ቦታውን ወይም አሠራሩን ሲለውጥ ወይም ቀድሞ የተሰጠውን ደረጃ ለማሻሻል ሲፈልግ አዲስ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ የማሕበራዊና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃውን ማስመደብ አለበት፡፡

፬/ በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚወጣ ወጪን አመልካቹ መሸፈን አለበት፡፡

9. <u>**Functions of a Validator**</u>

1/ A validator that has been registered by the Authority pursuant to this Regulation is entitled to perform the following functions:

a) examine and validate the environmental sustainability and social acceptability of the activities described in the documents submitted for certification;

b) examine the social and environmental management plan and validate the level of social and environmental compliance proposed by the applicant;

c) verify the capacity of an applicant to implement activities specified in the social and environmental management plan;

d) propose to the Authority the level of social and environmental compliance that should be awarded to the applicant;

e) submit an annual performance report to the Authority.

2/ The validator shall maintain records and documents pertaining to the implementation of this Regulation for a minimum of two years.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>CERTIFICATION</u>

10. <u>**Application for Certification**</u>

1/ Any farm is entitled to obtain a certificate if it is in compliance with the relevant requirements under this Regulation.

2/ A farm that applies for any certificate under this Regulation shall fill in an application form prepared by the Authority and submit it to the Authority together with its social and environmental management plan prepared by qualified experts as well as its financial audit report verified by a recognized independent auditor.

3/ A farm shall submit a new application to the Authority for the determination of its level of social and environmental compliance when it changes its location or processing facility or if it intends to modify the level of compliance previously awarded.

4/ Any cost incurred in association with certification under this Regulation shall be borne by the applicant.

**፲፩. የምስክር ወረቀት የመስጠት ውሳኔ**

፩/ ባለስልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሠረት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ማመልከቻ ሲቀርብለት አረጋጋጭን በመመደብ የሰነድ ምርመራ፣ የመስክ ጉብኝትና እንደአስፈላጊነቱም የናሙና ፍተሻ እንዲካሄድ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ለሚያሟላ እርሻ ባለሥልጣኑ የምሥክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ለእርሻው የምስክር ወረቀት ሲሰጥ እርሻው የደረሰበትን የማሕበራዊ እና የአካባቢ የኃላፊነት ደረጃ የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፍ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የማረጋገጫ ደብዳቤ የእርሻውን ስምና፣ አድራሻ፣ የእርሻውን ተወካይ ስም እና አድራሻ እና የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መግለፅ አለበት፡፡

፭/ እርሻው የሚጠበቅበትን መሥፈርት ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ማመልከቻ ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

፮/ ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ተቀባይነት ያላገኘለት እርሻ ይህንኑ ውሳኔ ካገኘበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ውስጥ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሌላ ማመልከቻ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

**፲፪. የምስክር ወረቀትን ስለማሻሻል**

፩/ ማንኛውም እርሻ ሥሙን ወይም የዋና ኃላፊውን ስም ሲለውጥ ወይም ማረጋገጫ የተሰጠውን የእርሻ ስፍራ ስፋትንም ሆነ የምርት ዓይነትን ሲጨምር፣ ሲቀንስ ወይም ሲያሻሽል፣ ወይም ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የማኅበራዊና የአካባቢ አያያዝ ዕቅዱን ሲቀይር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ ከሰጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የመቆያ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የሚችለው የታሰበው ለውጥ አስቀድሞ በሰጠው የምስክር ወረቀት በተዘረዘሩ ግዴታዎች የሚጠበቅ አፈፃፀምን የማይቀንስ ከሆነ ነው፡፡

**፲፫. የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

፩/ የእርሻውን የማሕበራዊ እና የአካባቢ ኃላፊነት ደረጃ የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆየው ለሁለት ዓመት ነው፡፡

፪/ የምስክር ወረቀት የተሰጠው እርሻ የተሰጠው የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከሦስት ወር በፊት የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስለት ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

**11. Decision of Certification**

1/ The Authority shall, upon receipt of an application for certification pursuant to Article 10 of this Regulation, assign a validator to commence document review, undertake on-site inspection and product testing as appropriate.

2/ The Authority shall grant a certificate if the farm is in compliance with the requirements of this Regulation.

3/ When a farm is granted a certificate, the Authority shall write a letter that specifies its level of social and environmental compliance.

4/ The evidence of certification, under sub-article (3) of this Article, shall state the name and address of the farm, the name and address of the contact person of the farm and the validity date of the certificate.

5/ The Authority shall reject an application when it is convinced that the farm does not comply with the requirements of the certification.

6/ A farm whose certification is withdrawn by the Authority shall not be allowed to make applications for certification within six months following the date of rejection under sub-article (5) of this Article.

**12. Modification of Certificate**

1/ Any farm shall inform the Authority when it changes its name or the name of its principal manager or when it modifies, reduces or expands the scope of a certified farm or product item or when it changes the approved social and environmental management plan.

2/ The Authority shall issue a replacement certificate with the same period of validity as the original certificate if it determines that the proposed changes would not reduce the quality of implementation of the terms and conditions set under the certificate issued to it previously.

**13. Validity Period of Certificate**

1/ A certificate attesting to the level of social and environmental compliance of a farm shall be valid for two-year.

2/ A farm holding a certificate shall submit a renewal application three months before the date of expiry of the certificate.

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም እርሻ ማሕበራዊ እና አካባቢያዊ የኃላፊነት ደረጃውን ስለመጠበቁ በየሁለት ዓመቱ በአረጋጋጭ መመዘን እና በባለሥልጣኑ እንደገና መረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የምስክር ወረቀት የሚታደሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተጠየቀው ማመልከቻ እንደገና ከተገመገመ እና ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

## ፲፬. የምስክር ወረቀት ያገኙ እርሻዎች ግዴታ

፩/ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እርሻዎች በዚህ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገጉ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ግዴታዎች መሰረት የራሳቸውን የውስጥ ኦዲት ማካሔድ አለባቸዉ፡፡

፪/ እያንዳንዱ እርሻ በማረጋገጫው ሂደት መጀመሪያ እና ከዚያም በኋላ በየሁለት ዓመቱ የተሟላ የውስጥ ኦዲት ማካሔድ አለበት፡፡

## ፲፭. የባለሥልጣኑ ተግባራት

፩/ ባለሥልጣኑ በአረጋጋጩ በሚቀርብለት ዘገባ መሠረት አግባብነት ያለውን የማሕበራዊ እና የአካባቢ ኃላፊነት ደረጃ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በመወሰን ለእርሻዎች የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የማሕበራዊ እና የአካባቢ የሃላፊነት ደረጃ የሚወስን የምስክር ወረቀት ለእርሻው ከመስጠቱ በፊት የመስክ ጉብኝት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ከነሐስ ደረጃ በታች ዝቅ ባሉ እርሻዎች ላይ አግባብነት ያለውን እርምጃ እንዲወስድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፪/፪ሺ ለተቋቋመው ለኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት በማረጋገጥ ተግባር ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ብቁ ድርጅቶች የሚያቀርቡ ለትን ማመልከቻ በመመርመር የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ መሟላት የሚገባቸውን የአካባቢ፣ የማሕበራዊ እና የጤና መሥፈርቶችን ለእርሻዎች ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት የተገለጹትን አገልግሎቶች ለመስጠት ብቁ የሆኑ አረጋጋጮች ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

3/ Every two years, farms shall be reevaluated by validators and rated by the Authority to re-verify their state of social and environmental compliance.

4/ A certificate shall be renewed after the renewal applications under sub-article (2) of this Article have been re-assessed and approved.

## 14. Obligations of Certified Farms

1/ Farms shall undertake their internal audits on the basis of environmental and social requirements set under this Regulation and under other pertinent laws.

2/ Each farm shall conduct a full internal audit at the initial stage of validation and every two years thereafter.

## 15. Role of the Authority

1/ The Authority shall, within five working days, issue the appropriate social and environmental compliance level and certify farms based on reports submitted by the valuator.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the Authority may take on-site inspections before issuing a certificate of social and environmental compliance level to the farm.

3/ The Authority shall inform the Ethiopian Horticulture Development Agency established by Council of Ministers Regulation No. 152/ 2008 to take appropriate actions on farms that fall below the Bronze Level Certification.

4/ The Authority shall issue a certificate of competence to firms that wish to engage in rendering validation services under this Regulation.

5/ The Authority shall notify any farm that asks for environmental, social and health requirements that must be fulfilled.

6/ The Authority shall keep a roster of validators that qualify for the provision of services under this Regulation.

፯/ ባለሥልጣኑ ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተከባሪነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

## ፲፮. ተቆጣጣሪዎች

፩/ የዚህን ደንብ መከበር የሚያረጋግጡ ተቆጣጣሪዎችን ባለስልጣኑ ሊመድብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ለተመደበ ተቆጣጣሪ ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ወረቀት በባለሥልጣኑ ኃላፊ ተፈርሞ ይሰጠዋል፡፡

፫/ ተቆጣጣሪው ሥልጣንና ተግባሩን በትጋትና ያለአድልዎ መፈጸም አለበት፡፡

፬/ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ሳይጠበቅበት ተቆጣጣሪው፡-

ሀ) የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እየተጣሱ ነው የሚያሰኘውን ምክንያት ሲያገኝ ወደ ማንኛውም የሥራ ቦታ ለመግባት፤

ለ) ምርመራ ለማካሔድና የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማዘዝ፤

ሐ) እርሻውን በማስተዳደር ላይ ካለ ከማንኛውም ሰው መረጃን ጠይቆ ለማግኘት፤

መ) የዚህን ደንብ ማናቸውም ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ተፈፅሞበታል ያለውን መሣሪያ፣ ማሕደር፣ ፅሑፍ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሠነድ በማስረጃነት መያዝ፤

ሠ) የማንኛውንም ቁስ ናሙናዎች እንደአስፈላጊነቱ ያለክፍያ መውሰድ እና መመርመር ወይም እንዲመረመሩ ማስደረግ ፤

ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፯. መረጃን ስለማጠናቀር

፩/ እርሻዎች የአካባቢ፣ የማሕበራዊና የጤና ግዴታዎችን ስለማክበራቸው ዓመታዊ ዘገባ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅፅ ማጠናቀርና ማቅረብ አለባቸው፡፡

7/ The Authority shall, in consultation with the Ministry of Labour and Social Affairs, the Ethiopian Horticulture Development Agency and other relevant government agencies, take all necessary actions to ensure the implementation and effectiveness of this Regulation.

## 16. Inspectors

1/ The Authority may designate inspectors to ensure compliance with this Regulation.

2/ Every inspector designated pursuant to sub-article (1) of this Article shall be given an identity card signed by the head of the Authority stating that he or she has been appointed as inspector.

3/ The inspector shall exercise due diligence and impartiality in the discharge of his powers and duties.

4/ The inspector may, without required to obtain a court order:

a) enter any place or facility in which he has reason to believe that a contravention of any provision of this Regulation is taking place;

b) inspect and order that corrective measures are taken as appropriate;

c) request to obtain information from any person in charge of the farm;

d) seize appliances, records, statements or other documents which may provide proof of contravention of any provision of this Regulation;

e) take free of charge samples of any material or substance as required and carry out or cause to be carried out tests as appropriate.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 17. Documentation

1/ Farms shall document all relevant reports on their state of compliance with environmental, social and health requirements; and shall provide an annual report based on the format prepared by the Authority.

፪/ እርሻዎች በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን ዘገባ የሚመለከቱትን ሠነዶቻቸውን በሥራ ቦታቸው ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ያህል ማቆየት እና ለተቆጣጣሪዎችም ክፍት ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ ሠነዶችን አለመስጠት ወይም በዚህ ደንብ ላይ የተጠቀሱ ተቆጣጣሪዎች ሥራን ማደናቀፍ አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔርና የወንጀል ሕጎች ያስጠይቃል፡፡

## ፲፰. መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭ መሠረት የተቋቋመው የአካባቢ ምክር ቤት ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ Farms shall place documents referred to under sub-article (1) of this Article at their respective sites for at least five years and make them available to inspectors.

3/ Failure to provide documents under this Regulation or to obstruct the undertakings of inspectors designated under this Regulation shall entail civil and criminal liability under the appropriate laws.

## 18. Power to Issue Directives

The Environmental Council established by Proclamation No.295/ 2002 may issue directives for the implementation of this Regulation.

## 19 Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazetta.

Done at Addis Ababa this 7[th] day of June, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት